እባክዎን ይህንን ምርመራ ፣ በተሸፈነ እና ደረቅ ባለ ቦታ ፣ እንዲሁም ከሕዝብ ቦታዎች ራቅ ባለ ቦታ ላይ ያድርጉት።

# የ COVID-19 የራስ-ምርመራ



## የቤት ውስጥ የ COVID - 19 የራስ ምርመራ ምንድነው?

በቤት ውስጥ ሊጠቀሙበት እና በ15 እስከ 30 ደቂቃዎች ውስጥ ውጤትዎን ማግኘት የሚችሉበት ፈጣን (አንቲጂን) ምርመራ ነው። ለ COVID-19 በጣም ለተጋለጡ ማህበረሰቦች በቀላሉ እንዲመረመሩ እና የበሽታውን ስርጭ ለመቀነስ በነፃ የራስ መመርመሪያዎችን እየሰጠን ነው።

## ምርመራውን መቼ ማድረግ አለብኝ?

ይሄንን የመመርመሪያ መሣሪያ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ይጠቀሙ፥

- የ COVID-19 በሽታ ከያዘው ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ከነበርዎ ወይም ከቤተሰብዎ ውስጥ አንድ ሰው ለ COVID-19 ከተጋለጠ ወይም ምልክቶች ካለበት
- ለስራ ወይም ለትምህርት ቤቶች - ምን አይነት ምርመራዎች ተቀባይነት እንዳላቸው፣ ከአሰሪዎ/ከትምህርት ቤቱ ጋር ያረጋግጡ
- ከቤተሰብ ስብሰባዎች፣ ድግሶች ወይም ከአመት በዓል ዥግጅቶች በፊት ወይም በኋላ
- እንደ የስፖርት ጨዋታዎች ወይም በእምነት ላይ የተመሰረቱ ትላልቅ ክስተቶች በኋላ እና ከጉዞ በኋላ

## የምርመራዩ ውጤት አዎንታዊ ከሆነ ምን ማድረግ አለብኝ?

- እቤትዎ ይቆዩ እና እራስዎን ለ10 ቀናት ከሌሎች ሰዎች ያግልሉ። እናም በቅርብ ለተገናኙዋቸው ሰዎች ያሳውቁ
- እራስዎን ለማግለል መቆያ/ማደሪያ ቦታ ከፈለጉ ወደ ኪንግ ካውንቲ COVID-19 የጥሪ ማእከል ይደውሉ፤ 206-477-3977*
- እራስዎን በሚያገሉበት ወቅት የአስፔዛ ፣ የሂሳብ ክፍያዎችን ወይም የሌሎች አስፈላጊ ነገሮች እርዳታ ለማግኘት ወደ እርዳታ ማስተባበሪያ ማእከል ይደውሉ ፤ 206-477-8260*
- ስለ ጤናዎ ወይም ስለ COVID-19 ምልክቶች ጥያቄዎች ወይም ሃሳቦች ካልዎት፣ ሃኪሞትን ያነጋግሩ
- የምርመራ ወጤትዎን ለዋሽንግተን ግዛት ጤና መምሪያ ያሳውቁ፤ 1-800-525-0127*
- ለተጨማሪ መረጃያ፣ kingcounty.gov/nextsteps ይጎብኙ።



*ከላይ ለተዘረዘሩት ስልክ ቁጥሮች የቋንቋ ድጋፍ ለማግኘት፣ ጥሪውን በሚያደርጉበት ጊዜ ፣ የሚፈልጉትን ቋንቋ ይናገሩ።

### በሚመለከቱት ሁኔታዎች ላይ የፈጣን የራስ ምርመራ ተቀባይነት የለውም፥

- የጉዞ መስፈርቶችን ለማሟላት
- የኳራንቲን ጊዜዎችን ለማሳጠር
- የክትባት ማረጋገጫ ወደሚያስፈልጋቸው ተቋማት ለመግባት

**የምርመራ ውጤትዎን ከመመርመሪያ ጣቢያ እየጠበቁ ከሆነ ይህንን የመመርመሪያ መሣሪያ አይጠቀሙ።** ውጤትዎን ይጠብቁ እና መመሪያዎችን ይከተሉ።

**ስለ ምርመራው ተጨማሪ መረጃ kingcounty.gov/selftest ይጎብኙ።**

Public Health
Seattle & King County